5ኛ ዓመት ቁጥር 30
5th Year Nº 30

ባህር ዳር ህዳር 10 ቀን 1991
Bahir Dar 19th Nov. 1998

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ
ZIKRE HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE
IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 1.65	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ	የፖ.ሣ.ቁ 312 P.o.BOX

ማ ው ጫ	CONTENTS
አዋጅ ቁጥር 30/1991 ዓ.ም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብርን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ገጽ 8	Proclamation Nº 30/1998 A Proclamation To Provide for the Rural Land Use Fee and Agricultural Activities Income Tax in the Amhara National Regional State. page 8

አዋጅ ቁጥር 30/1991 ዓ.ም
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብርን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

በሥራ ላይ ያለው የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 77 /1968 /እንደተሻሻለ/ የእርሶአደሩን የመክፈል አቅምና የእርሻ ሥራ የሚገለገልበትን የመሬት ይዞታ መጠን ያላገናዘበ ስለሆነ ከክልሉ መንግስት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ጋር የማይጣጣም በመሆኑ ፣

ይህን ሁኔታ ለመለወጥ እንዲቻል ሚዛናዊ የሆነ የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር አከፋፈል ስርዓት በመዘርጋት

PROCLAMATION Nº 30/1998
A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE RURAL LAND USE FEE AND AGRICULTURAL ACTIVITIES INCOME TAX IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE

WHEREAS the existing Rural Land Use Fee and Agricultural Activities Proclamation Nº 77/1976 does not give due consideration to financial positions of farmers, the size of land each holds and is inconsistent with the economic policy of the state;

WHEREAS to bring an end to this state of affairs it has been found essential to reasonably set the payment for the Rural Land

ገቢ ለማሣደግ የሚያስችል አዲስ ህግ ማውጣት በማስፈለጉ ፣

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ህገ መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ መሠረት የሚከተለውን አውጿል።

ክፍል አንድ
ጠ ቅ ላ ላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ''በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 30/1991'' ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

1. ''የገጠር መሬት''ማለት በማዘጋጃ ቤት ወይም አግባብ ባለው አካል ከተማ ተብሎ ከተሰየመ ክልል ውጭ የሚገኝ መሬት ነው።

2. ''አርሶ አደር '' ማለት ለንግድ ሳይሆን በዋነኛነት የራሱን መሠረታዊ ፍላጎቶች ለማሟላት የእርሻ ሥራ የሚያካሂድ ሚናቸውም በግል የሚሠራ ሰው ወይም የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማኅበር አባል ሆኖ በወል የሚሠራ ሰው ነው።

3. '' የህብረት ሥራ ማኅበር '' ማለት በአርሶ አደሮች የኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 25/1990 መሠረት የተደራጀ የአርሶአደሮች ኅብረት ሥራ ማኅበር ነው።

4. '' ክፍያ '' ማለት በዚህ አወጅ መሠረት ከአርሶ አደሩ የእርሻ መሬት የሚጠየት የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ ነው።

5. ''የገቢ ግብር'' ማለት የመሬት ይዞታ መጠንን መሠረት በማድረግ ከእርሻ ሥራ በሚገኝ ገቢ ላይ ተወስኖ የሚከፈል ግብር ነው።

6. '' የመሬት ይዞታ'' ማለት በአንድ አካባቢ ወይም በተለያዩ ቦታዎች ሆኖ በአርሶ አደር ስም የተመዘገበና ለእርሻ ሥራ የተያዘ መሬት ሲሆን ወጀድን ይጨምራል።

7. ''ግብር ሰብሳቢ '' ማለት የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር እንዲሰበሰብ በሚመለከተው የቀበሌ አስተዳደር የሚወከል ሰው ነው።

Tax in order to increase income; it is found necessary to have a new proclamation;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 49 (3) (9) of the Constitution of the Amhara National Regional State, it is hereby proclaimed as follows:

PART ONE
GENERAL PROVISIONS

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Amhara National Regional State Rural Land Use Fee and Agricultural Activities Income Tax Proclamation No30/1998."

2. Definition

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1."Rural Land" shall mean all land outside the boundaries of a municipality or outside an area designated as town by an appropriate body.

2."Farmer" shall mean an individual or is a member of a farmers' agricultural co-operative who earns his living by farming.

3."Cooperative" shall mean a farmers' agricultural cooperative organized in accordance with proclamation 25,1998.

4. "Fee" shall mean fee payable for rural land use.

5. "Income Tax" shall mean tax payable on income from agricultural activities.

6. "Land Holding" shall mean any land on one or different areas registered by the name of a farmer for agricultural activities including garden area.

7. "Tax Collector" shall mean any Kebele Administration or any person authorized by Kebele Administration to collect land use fee and income tax.

8. ''ግብር አስገቢ መ/ቤት '' ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብ ቢሮ ነው።

9. ''ቢሮ '' ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብ ቢሮ ነው

10. ''መንግስት '' ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ነው።

ክ ፍ ል ሁ ለ ት

ስለገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ

3. የገጠር መሬት መጠቀሚያክፍያን ስለማስከፈል

ማንኛውም አርሶ አደር ለያዘው የገጠር መሬት አገልግሎት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 የተመሰነውን የመጠቀሚያ ክፍያ የመክፈል ግዴታ አለበት።

4. ስለ መጠቀሚያ ክፍያ ተመን

1. በአማራ ብሔራዊ ክልል የሚገኝ ማንኛውም አርሶአደር የሚከፍለው ዓመታዊ የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ ተመን እንደሚከተለው ተወስኗል።

ተ.ቁ	የመሬት ይዞታ መጠን/በሄ/ር/	የክፍያ መጠን /በብር/
1	እስከ 0.5	10
2	ከ 0.5- 1.0	12
3.	ከ 1.0 - 1.5	14
4	ከ 1.5 - 2. 0	16
5	ከ 2.0 - 2.5	18
6	ከ 2.5 በላይ	20

2 .በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም የክልሉ መንግስት ባወጣው የምግብ ዋስትና መርሐ ግብር ስታቀፉ ቀበሌዎች የሚኖር አርሶአደር የሚከፍለው ዓመታዊ የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ እንደሚከተለው ይሆናል።

ተ.ቁ	የመሬት ይዞታ መጠን/በሄ/ር/	የክፍያ መጠን በብር/
1	እስከ 0.5	8

8. "Tax Office" shall mean the Amhara Finance Bureau, the Zonal or the Woreda finance office.

9. "Bureau" shall mean the Amhara National Regional State Finance Bureau.

10. " State" shall mean the Amhara National Regional State.

PART TWO

RURAL LAND USE FEE

3.Rural Land Use Payment of Fee

Rural land held for agricultural activities shall be subject to land use fee in accordance with this proclamation article 4.

4. Rate of Fee

1. Every farmer in the region shall pay rural land use fee as indicated below.

No.	Land holding size in hectare	Income Tax Eth. Br.
1.	Upto 0.5	10
2.	0.5- 1.0	12
3.	1.0 - 1.5	14
4.	1.5 - 2.0	16
5.	2.0- 2.5	18
6.	over 2.5	20

2. Notwithstanding the provision of Sub Article 1 of this Article farmers embraced by the region's food security program shall pay the land use fee at the following rate.

No.	Land holding size in hectare	Income Tax Eth. Br.
1.	Upto 0.5	8

~~238~~ ~~238~~ 238 238

2	ከ0.5 -1.0	10
3	ከ1.0 -1.5	12
4	ከ1.5- 2.0	14
5	ከ2.0- 2.5	16
6	ከ2.5 በላይ	18

5. ስለ ግዴታዎች

1. ማንኛውም አርሶ አደር በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 4 ስር የተወሰነውን ክፍያ በአዋጁ አንቀጽ 6 ስር በተገለፀው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለግብር ሰብሳቢው የመክፈል ግዴታ አለበት

2. ማንኛውም አርሶአደር የመሬት ይዞታ መጠኑን ለቀበሌው መስተዳድር የማሳወቅና ትክክለኛነቱንም የማረጋገጥ ግዴታ አለበት።

6. ስለ ክፍያ መሰብሰቢያ ጊዜ

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚጠየቅ የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ የሚሰበሰበው በጠጅት ዓመቱ ከጥቅምት 1 እስከ ሚያዚያ 3ዐ ባለው ጊዜ ውስጥ ይሆናል።

7. ስለ ግብር ሰብሳቢው ግዴታ

ማንኛውም ግብር ሰብሳቢ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 መሠረት የሰበሰበውን የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ ገንዘብ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ለሚመለከተው ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት ገቢ የማድረግ ግዴታ አለበት።

ክ ፍ ል ሶ ስ ት
ስለእርሻ ሥራ ገቢ ግብር አከፋፈል

8. የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ስለመክፈል

ማንኛውም አርሶ አደር ከተሠማራበት የእርሻ ሥራ በሚያገኘው ገቢ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 ላይ የተወሰነውን ዓመታዊ የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት።

9. ስለእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ክፍያ ተመን

1. በኢሚራ ብሔራዊ ክልል የሚገኙ ማናቸውም አርሶአደር የሚከፍለው ዓመታዊ የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ክፍያ ተመን እንደሚከተለው ተወስኗል።

2.	0.5- 1.0	10
3.	1.0 - 1.5	12
4.	1.5 - 2.0	14
5.	2.0- 2.5	16
6.	over 2.5	18
7.		

5. Obligations

1. Every farmer is hereby obliged to pay the land use fee to the tax collector within the time schedule in accordance with Article 6 of this proclamation.

2. Every farmer is hereby obliged to notify and assure his/her land holding size to his/her Kebele Administration.

6. Time of payment

Rural land use fee shall be collected between Tikemt 1 and Miazia 30 (October 9 and May 8) of every year.

7. Obligation of Tax Collectors

Every tax collector is obliged, in accordance with Article 6 of this proclamation, the fee he collects, to submit to the concerned woreda finance office based on the directive the bureau issues.

PART THREE

AGRICULTURAL INCOME TAX

8. Payment of Agricultural Income Tax

Every farmer is obliged to pay agricultural income tax for the income he/she generates from agricultural activities in accordance with Article 9 of this proclamation

9. Rate of Agricultural Income Tax

1. Every farmer in the region shall pay according the following schedule.

ተ.ቁ	የመሬት ይዞታ መጠን/በሄ/ር/	የክፍያ መጠን በብር/
1.	እስከ 0.5	10
2.	ከ0.5 -1.0ዐ	13
3.	ከ1.0 -1.5	16
4.	ከ1.5- 2.0	19
5.	ከ2.0- 2.5	22
6.	ከ2.5 በላይ	25

2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም የክልሉ መንግስት ባወጣው የምግብ ዋስትና መርሐ ግብር በታቀፉ ቀበሌዎች የሚኖር አርሶአደር የሚከፍለው ዓመታዊ የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ክፍያ እንደሚከተለው ይሆናል።

ተ.ቁ	የመሬት ይዞታ መጠን/በሄ/ር/	የክፍያ መጠን በብር/
1.	እስከ 0.5	5
2.	ከ0.6 -1.0	8
3.	ከ1.0 -1.5	11
4.	ከ1.6- 2.0	14
5.	ከ2.1- 2.5	17
6.	ከ2.5 በላይ	20

10. የክፍያና ግብር ተመን ስሌት መሠረት

የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር መጠን ተሠልቶ የሚወሰነው እያንዳንዱ አርሶአደር ባለው የመሬት ይዞታ መጠን ላይ ተመሥርቶ ይሆናል።

11. ስለ ግዴታዎች

ማንኛውም አርሶአደር በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 9 የተወሰነውን ክፍያ በአዋጁ አንቀጽ 12 ሥር በተገለፀው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለግብር ሰብሳቢው የመክፈል ግዴታ አለበት።

12. ስለ ገቢ ግብር መሰብሰቢያ ጊዜ

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚጠየቅ የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር የሚሰበሰበው በበጀት ዓመቱ ከጥቅምት 1 እስከ ሚያዚያ 3ዐ ባለው ጊዜ

No.	Land holding size in hectare	Income Tax Eth. Br.
1.	Upto 0.5	10
2.	0.5- 1.0	13
3.	1.0 - 1.5	16
4.	1.5 - 2.0	19
5.	2.0- 2.5	22
6.	over 2.5	25

2. Notwithstanding the provision of Sub Article 1 of this Article farmers embraced by the Regional Food security Program shall pay the Agricultural Income Tax at the following rate.

No.	Land holding size in hectare	Income Tax Eth. Br.
1.	Upto 0.5	5
2.	0.5- 1.0	8
3.	1.0 - 1.5	11
4.	1.5 - 2.0	14
5.	2.0- 2.5	17
6.	over 2.5	20

10. Base of Payment

The base for the payment of rural land use fee and agricultural income tax is size of land holding of each farmer.

11. Obligations

Every farmer is obliged to pay the income tax as mentioned by Article 12 of this proclamation.

12. Time of Income Tax Collection

The income tax levied according this proclamation shall be collected between Tikemt 1 and Miazia 30 (October 9 and

240 240

ውስጥ ይሆናል።

13. ስለ ግብር ሰብሳቢው ግዴታ

ማንኛውም ግብር ሰብሳቢ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 መሠረት የሰበሰበውን የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ገንዘብ ቢሮ በሚያወጣው መመርያ መሰረት ለሚመለከተው ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት ገቢ የማድረግ ግዴታ አለበት።

ክ ፍ ል አ ራ ት
ግብር አስገቢ አካላት ሥልጣንና ተግባር

14. ስለ ግብር ሰብሳቢው

በዚህ አወጅ መሠረት የተወሰነውን ክፍያና ግብር የሚሰበስበው እያንዳንዱ የቀበሌ መስተዳድር ከቀበሌው ውስጥ ውስጥ መርጦ የሚወክለው ሰው ይሆናል።

15. የአርሶአ ደሮችን ዝርዝር ስለማሳወቅ

ማንኛውም የቀበሌ አስተዳደር በቀበሌው ውስጥ የሚኖሩ አርሶአደሮችን ስም ዝርዝር ከመሬት ይዞታ መጠናቸው ጋር በየበጀት ዓመቱ ከመስከረም 30 ቀን በፊት ለወረዳው መስተዳድር የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

16. ስለ ወረዳው መስተዳድር ኃላፊነት

እያንዳንዱ የወረዳ መስተዳድር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 የተላከለት ዝርዝር እንደደረሰው ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ ለወረዳው ግብር አስገቢ መ/ቤት ያስተላልፋል።

17. ስለ ወረዳ ግብር አስገቢ መ/ቤት ግዴታ

የወረዳው ግብር አስገቢ መ/ቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 መሠረት የተላለፈለትን ዝርዝር ከአስገባው ዓመታዊ ገቢ ጋር አመሣክሮ ውጤቱን ለወረዳው መስተዳድር የማሳወቅ ኃላፊነት አለበት።

18. ስለ ውሳኔ አፈፃፀም

ማንኛውም አርሶአደር የተወሰነበትን

May 8) of every year.

13. Obligation of the Tax collectors

Every tax collector is obliged, in accordance with Article 12 of this proclamation, the income fax he collects, to submit to the concerned Woreda Finance Office based on the directive the bureau issues.

PART FOUR
POWER AND DUTIES OF TAX OFFICE

14. Tax Collector

Every kebele Administration can assign anyone within to collect the fee and the income tax as stated by this proclamation.

15. Submission of Farmers' List

At the coming into force of this proclamation every Kebele Administration shall annually submit the list of farmers and the size of their holding residing within the keble to the concerned Woreda Finance Office before the 30th of Tikimt (9th of November).

16. Responsibilities of the Woreda Coucil Office

Every Woreda Council Office shall check and send the list of farmers it receives as per Article 15 of this proclamation to its woreda Finance Office.

17. Duties of Tax Office

Every Tax Office shall check if the actual revenue collected is as per the farmers list described by Article 16 of this proclamation and shall submit a performance report to its respective Woreda Council Office at the end of collection period.

18. Execution Proceedings

Every Kebele Administration may initiate

241

የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የገቢ ግብር በአዋጁ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሳይከፍል የቀረ እንደሆነ የመክፈያው ጊዜ ካለፈበት ቀን ጀምሮ በማናቸውም ጊዜ የቀበሌ አስተዳደሩ በሚመለከተው የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት ክስ መሥርቶ የማስፈፀሚያ ትዕዛዝ ሊያሰጥበት ይችላል።

19. ደረሰኝ ስለመስጠት

1. ማንኛውም አርሶአደር በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚፈፅመው ክፍያና የገቢ ግብር ከግብር ሰብሳቢው ህጋዊ ደረሰኝ የማግኘት መብት አለው።
2. በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከፈል ክፍያና የገቢ ግብር የሚሰበሰበው ቢሮው በሚያዘጋጀው የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ብቻ ይሆናል።

ክ ፍ ል አ ም ስ ት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች፤

20. ስለ መቀጫ

ማንኛውም አርሶአደር በዚህ አዋጅ መሠረት ሊከፍል የሚገባውን የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የገቢ ግብር በአወጁ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ሳይከፍል ከቀረ ክፍያው ወይም ግብሩ በዘገየበት በእያንደንዱ ወር የግብሩን ሁለት በመቶ /2%/ መቀጫ ይከፍላል። ሆኖም የመቀጫው መጠን ከግብሩ ሃያ አምስት በመቶ /25%/ መብለጥ የለበትም።

21. ስለ አበል

የቀበሌ መስተዳድር በዚህ አዋጅ መሠረት ከሰበሰበው ገንዘብ ውስጥ ሶስት በመቶ/3%/ በኮሚሽን መልክ ይሰጠዋል። ክፍፍሉን በተመለከተ ደንብና መመሪያ ሊወጣ ይችላል።

22. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚረዱትን ደንቦች የማውጣት ስልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብ ቢሮ የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ለማውጣት ይችላል።

an execution proceeding before the Kebele Social court against a farmer who fails to effect payment according the duration of payment.

19. Giving Receipts

1. Every farmer has the right to get a receipt for what he pays from the tax collector.
2. Land use fee and income tax in accordance with this proclamation shall be collected by the receipt the bureau produces.

PART FIVE

MISCELLANEOUS PROVISIONS

20. Penalties

Any farmer who, within the period specified by this proclamation, fails to pay the income tax or fee imposed on him in accordance with this proclamation shall pay a penalty of two percent (2%) of the amount of tax or fee in respect of every month during which payment is in default, upto a maximum penalty of 25%.

21. Remuneration of Services

Every Kebele Administration shall be paid three percent (3%) of the collection it has made in accordance with the provisions of this proclamation in consideration of its services. A regulation or directive may be issued on its distribution.

22. Power to Issue Regulations and Directives

Regulations by the Executive Committee of the Region, and directives by the Bureau may be issued for the purpose of the implementation of this proclamation.

~~238~~ ~~239~~ 242 242

23. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ይህንን አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት የሚወጣውን ደንብ ወይም መመሪያ በሥራ ላይ በማዋል አረገድ የመተባበር ግዴታ አለበት።

24. ስለ ወንጀል ቅጣት

ይህንን አዋጅ ወይም በአወጁ መሠረት የሚወጣውን ደንብ ወይም መመሪያ የተላለፈ ማናቸውም ሰው አግባብ ባለው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ መሠረት ይቀጣል።

25. ተፈፃሚነት ስለማይኖረው ህግ

1. የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር አዋጅ 77/1968 /እንደተሻሻለ/ ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ በአማራ ብሔራዊ ክልል ውስጥ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሌላ ህግ ፣ ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዩች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

26. አዋጅ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ምክርቤት
ህዳር 10ቀን 1991 ዓ.ም.
ባህርዳር

23. Duty to Co-operate

Any individual or legal body is bound to cooperate in the carrying out of the provisions of this proclamation and regulations or directives to be issued in persuance of this proclamation.

24. Criminal Penalties

Anyone who violates the provisions of this Proclamation or regulations and directives to be issued in persuance of this proclamation shall be punishable in accordance with Penal Code.

25. Inapplicable Laws

1. Beginning from the effective date of this proclamation the Rural Land Use Fee and Agricultural Activities Income Tax Proclamation No. 77/1976 (as amended) shall have no effect on matters provided for under this proclamation.

2. Any law, regulation or directive which is inconsistent with this Proclamation shall not apply with respect to matters provided for in this Proclamation.

26. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of its ratification by the council of the Amhara National Regional State.

Done at Bahir Dar

This 19th day of November, 1998

The Council of the Amhara National

Regional State

243

243